# ዛሬም እንደገና

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር February 28, 1933 በአምባገነንነት ስልጣን የተቆናጠጠው ሂትለር የDachau, Buchenwald, Sachsenhausenና Ravensbruck ማጎሪያወችን ለመክፈትና ጭፍጨፋውን ለመጀመር የጨረሰበት 23 ቀናቶች ብቻ ነበሩ። እጅግ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ከ6 ሚሊዮን በላይ ንጹሃንን እንደ ወረርሽኝ በሽታ በአሰቃቂ መልኩ ሲያጭድ April 1945 የራሱ ተራ መሆኑን በውል አልተገነዘበም ነበር።

ንጹሀንን በአምባገነንነትና በጭካኔነት ጨፍጭፎ የንጹሀንን ደም አፍሶና የዜጎችን መሰረታዊ ህይወት አናግቶ የግልን ህይወት በሰላም መቀጠል ህልም በመሆኑ እስከ August 14, 1961 ናዚዎች እንደዱር ድኩላ እየታደኑ በህይዎት ያሉት ሁሉ ለፍርድ መቅረባቸዉና እንደወነጀላቸው መጠን ቅጣት መቀበላቸዉን በMay 31, 1962 በRamleh በስቅላት የተቀጣው የግፈኛው ፋሽሽት የEichmann እስትንፋስ ቀነ-ፍጻሜ ያሰረዳናል።

ዛሬ በሀገራችን ኢትዮጵያ እንደተከሰተውና እንደነመንግስቱ ሐይለማርያምና መላኩ ተፈራ አይነት አረመኔዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ November 20, 1945 በNuremberg አለም አቀፍ የወታደር ፍርድ ቤት 21ዱ ከፍተኛ የሂትለር ባነስልጣኖች ለፍርድ ሲቀርቡ ሁሉም በአንድ ቃል ያቀረቡት መከላከያ ቢኖር ህይወት አላጠፋንም እኛ ታዛገሮች ነበርን የግድያ ትእዛዝ ሁሉ የተሰጠው በአዶልፍ ሂትለር ነው የሚል የክህደት ምላሽ ነበር። ነገር ግን ለፍርድ ቤቱ በቀረበ የአይን ምስክሮች የፊልምና የጹሁፍ ማስረጃዎች መስረት 21ዱም ወንጀለኞች October 16, 1946 ለፍርድ በቀረቡ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በNuremberg እስርቤት በስቅላት ተቀጥተው በድናቸው ተቃጥሎ አመዱ በMunich ተበትኗል።

እንደትናንቱ የስታሊን እብደት የሂትለር ጭፍጨፋ የማኦ የባህል አብዮት የፖልፖት ሽብር የሳዳም ርህራሄ ቢስ ግድያ የኢዲያሚንና ሞቡቱ ሴሴሴኮ እብደት ሁሉ እኛ ኢትዮጵያዊያንም በኢሰፓና አጋሮቹ የዘር ማጥፋት እብደት ከ1977 እስከ 1991 በእብሪት ተጨፍጭፈናል። በነምስራቅ ጀርመን ኩባና ሶቭየት ህብረት እየታገዙ ንጹሀንን ያለፍርድ ጥያቄና ርህራሄ ጨርሰዋል። ክቡር የሰው ልጅ ገላ እንደ ቆሻሻ በየአውራ ጎዳናው ተጥሏል። የሚች ቤተሰቦች አስከሬን በገንዝብ ገዝተዋል። ከ1984 እስከ 1987 በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖች ሰሚ ጠፍቶ በረሀብና በበሽታ አልቀዋል። መንግስቱና አጋር ሹሞቹ ከማኦ ሰታሊን ሳዳምና ፖልፖት ቀጥለው ቢያንስ የ1.7 ሚሊዮን ንጹህ ዜጎችን ህይወት ቀንጥሰዋል።

"ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ" ነውና ዛሬ ሀቁ ተደብቆ በምትኩ በኢሰፓና መሰሎቹ የተቀነባበረ ሰቅጣጭና ዘግናኝ መከራና ችግር የተመላበት የማስመሰያ ትያትር እያየን እንገኛለን። ወቅቱ ተቀይሮ ጊዜ ፈርዶባቸው አሳዳጆቹ ተሳዳጅ ሆኑ። ገዳዮቻችን በከፊል ለፍርድ ቀረቡ። አብዛኛዎቹ ሀገር ለቀው ፈረጠጡ። ያለቅጥና መጠን የተፈለፈሉት የደርግ ካድሬዎች ከነመርዛቸው በመላው አለም ተበተኑ። "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" ሆነና ኢሰፓ ለኢትዮጵያ አንድነት አሳቢ ለኢኮኖሚ ፖለቲካና ማህበራዊ እድገት ብቸኛ ተቆርቋሪ በመሆን ለዘመናት የምናውቀውን ካባ አውልቆ ሌላ አሳሳችና ቆሻሻ በርሮስ ተላብሶ መፈራገጥ ጀመረ። የአንድ ሰሞን ወዳጆቹን እነመኢሶን ማሌሪድ ኢጭአት ወዝሊግና ሰደድን እንዲሁም የቅርብ ጊዜ አጫፋሪዎቹን እነኢህአፓን ከየጎጡ አሰባስቦ ካደሬዎቹን በተሀድሶ አስዉቦ የአዞ እንባውን በማዝነብ ላይ ይገኛል።

September 12, 1984 ብቸኛና ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ በሰባቱ አውራ የደርግ አምባገነን ወታደሮች በአራት የታሪክ እጣቢ ሲቪሊያን በስድስት ለሆዳቸው ያደሩ ተለዋጭ አባላትና በ835 አሳማ የብሄራዊ ሸንጎ አባላት የበላይነት የተቋቋመው ኢሰፓ በMay 1991 ተፈረካክሶ እስኪበታተን ድረስ እጅግ ዘግናኝና አጸያፊ ድርጊቶችን ፈጽሟል። አገራችን de facto single-party State በማድረግ ቀጥቅጦ የገዛን አምባገነን ሀይል ዛሬ ቅንጅት ሆኖ ስለ ዲሞክራሲ ሊያስተምረን ይፍጨረጨራል።

የትናንቱ ቀይሽብር ፈጣሪና አቀነባባሪ POMOA (የመኢሶንና ደርግ ቅይጥ ገደይ ቡድን) በሀይሌ ፊዳና ነገደ ጎበዜ እየተመራ በ1979 ከመካከላቸው በበቀለው የመንግስቱ ሀይለማሪያም ልዩ ፓርቲ (አብዮት ሰደድ) እየታደነ ከሀገር እስኪባረር ድረስ ትውልድን በጅምላ የጨፈጨፈ የታሪክ ተዎቃሽና ተከሳሽ ቡድን ነው። በሀይሌ ፊዳ ነገደ ጎበዜ አክሎክ ቢራራና መሰል አጋሮቻቸው አስተባባሪነት ከ1977 እስከ 1978 በጅምላ ግድያ የተጨፈጨፉት ግምታቸው ከአምስት ሽህ የማያነሱ ወገኖች ብቁ ማስረጃ ናቸው። ነገደ ጎበዜና እሸቱ ጮሌ ከእውቁ ሶሻል ሳይንቲስት አንድሬ ጉንዳር ፍራንክ የጨለፉትን የወታደራዊ አገዛዝ ጽንሰ-ሀሳብ መርህ በማድረግ "ኢትዮጵያ በተደራጀና ጡንቻ ባለው ወታደር ካልተገዛች የወቅቱ ለውጥ ብዙ አይጓዝም" በማለት ለእርድ አሳልፈው የሰጡን የሀገርና የወገን ጠላቶች ናቸው። የስታሊን ቀይ ጉላ በማለት ቀይ ሽብርን አውጀው ደርግን ጭፍጨፋና ግድያ ያስተማሩ አጋንንቶች ናቸው። የዛሬን አያርገዉና ኢህአፓ ይህን የማይበጅ ሀሳብ አጥብቆ በመቃወም እነደሻማ እንቀልጥ ዘንድ ግብታዊ በሆነ መንገድ ለእርድ ዳርገውን ነበር።

ዛሬ ያ ሁሉ እልቂት ተረሳና ገዳይ ተወድሶ ሟች የሚወቀስበት ገራፊ ተመስግኖ ተገራፊ የሚወገዝበት አሳዳጅ ተከብሮ ተሳዳጅ የሚዘለፍበት ዘመነ-ቅንጅት ደረስን። "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" እንዲሉ የካሳ ከበደ ከኢትዮጵያ ህዝብ በተዘረፈ ንብረት የደለበ ካዝና ተከፍቶ ካድሬዎች እንዲያቅራሩ ሚዲያ ተዘረጋ። መሰንበት ደግ ነውና በኢህአፓና መኢሶን የማይውል የማያድር ጋብቻ ስንገረም ደርግ በታንክ ጨፍልቆ የእድሜ ልክ የተሽከርካሪ ወንበር ሰለባ ያደረገው ዶ/ር ጌታቸው ሀይለ ሳይቀር ሀቁን ሊያስክደንና ጠላቶቻችን ጋር ሊያዋግነን ብሎም የራሱን የስልጣን ወንበር ከወዲሁ ሊያመቻች ሲፍጨረጨር አየን ሰማን። የኢዩቬልዩ ፍቅር እረፍት የነሳቸው ሁሉ አፍቅሮተ-ስልጣን ሲያቅበዘብዛቸው ተመለከትን።

እንደምናውቀው ሁሉ ኢሰፓና መሰሎቹ በግፍ የህዝብን ደም አፍሰው ዜጎችን በእስር ቤቶች አጉረው ወገንን በረሀብ በሽታና ጦርነት ጨርሰው ለራሳቸው ድሎትና ደስታ የተፈጠሩ ካድሬዎቻቸው እንዳሻቸው በህዝብ ደም ዋኝተው ወቅቱ ሲደርስ ተዋርደውና አፍረው ከስልጣን የኮበለሉ እኩይ ፍጡር ናቸው። ይህን አሰቃቂ ተግባራቸውን እንደገና ለመመለስ መሰሪ ጠበብቶቻቸውን አሰባስበው ሀገርና ወገንን አፍቃሪ በመምሰል ዛሬም እኛ የምንነግራችሁን ብቻ አድምጡ ይሉናል። ለመጭው የሀገራችን ሰላም እድገትና ብልጽግና ብቸኛው አማራጭ የነገደ ጎበዜ ሰውር ደባ ብቻ እነደሆነ አድርገው ይሰብኩናል። በቀንደኛ መኢሶንነቱ ንጹሃንን እንዳሸነ ያረገፈዉን አበራ የማናብን እርግብ ነው ይሉናል። በስልጣን ዘመኑ ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ድምጹ ያልተሰማውን ሀይሉ ሻወልን ለኢትዮጵያ ከሰማየ ሰማያት የወረደ መድሃኒት አስመስለው ያቀርቡልናል።

እነኚህ የገንዘባቸውና የአምባገነንነታቸው ብዛት የማነአለብኝነታቸውና የደደብነታቸው ጥልቀት የሰልጣናቸውነና የሀይላቸው ምጥቀት ከመጨረሻው ምልዕት ደረሶ

ወደዲያቢሎሳዊ ባህርይ ያሸጋገረቸው ኢሰፓዊያንና ጎበዝያን (የነገደ ጎበዜ አጫፋሪዎች) ሲጠፉ ሲቃጠሉና ሲወገዱ መመልከቱ ደስታንና እርካታን የሚፈጥርልን ኢትዮጵያዊያን እነዳለን ተዘንግቶ ዛሬ የደርግ የክፉ ቀን ልጆች በሀይሉ ሻወል መሪነት ካቢኔ ሰይመው እንደገና ለፍዳ ሊዳርጉን ሲዘጋጁ እኛ ኢትዮጵያዊያን እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል። ቅንጅት በሚል የገዳዮች ውህደት ተሰባስበው ተግባራቸው ለሰሚ የሚዘገንን የኢሰፓና መኢሶን ነብሰ-ገዳዮች አመራሩን ተረክበው መከራችን ሊያራዝሙ የሚያደርጉት ሙከራ ሊወገዝ ይገባዋል። ቱባ ሹመት በያዙበት ወቅት ያሰሩንና የገደሉን የኢሰፓና መኢሶን ዉድ ልጆች ከጭንቅ የተረፈውን ትውልድ እንደገና በቀይ ማጭዳቸው ሊያጭዱን ሲያኮበክቡ ማውገዝና መፋለም አማራጭ የሌለው የንጹህ ዜግነት ግዴታችን ነው።

በአብዛኛው የፖለቲካ መድረክና ውይይት ስለቀይና ነጭ ሽብር አሰቃቂነት በተደጋጋሚ ብንሰማም ቅንጅት አይናችን በራፌ ጨርቅ ሸፍሮ ጆሯችን በጥጥ ወትፎ በሀይሉ ሻወልና (የመንግስት እርሻ ሚኒስትር) በካሳ ከበደ (የሰራተኞችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒሰትር) በትረ-ስልጣን ወቅት ወገንን እንደ አሸን ያረገፈው "አረንጓዴ ሽብር" እንዳይሰማ ብርቱ ጥንቃቄ ሲያደርግ ይታያል። በደርግ ሰልጣነ-መንግስት ከነነገደ ጎበዜና ሀይሌ ፊዳ ቀይሽብርና ነጻ እርምጃ በተኣምር ህይወቱ የተረፈውን ሰርቶ-በሌና ገበሬ ሀይሉና ካሳ ተረክበው ያለ ፈቃዱ በጠመንጃ አፈሙዝ አስገድደው በየበርሃው በማጎር የጨረሱት ውድ ህይወት በቀላል አሀዝ የሚገመት አይደለም። በምስሌነት ከሚጠቀሱት የእርሻ ማጎሪያወች አንዱና ዋነኛው ሁመራ እርሻ ልማት ነው። ከ1972-1973 በአንድ የጥፋት አመት ከ20 ሺህ በላይ የሆነ ተገዶ ዘማች እንደቅጠል ረግፏል። በወቅቱ የሁኔታው አሳሳቢነትና በየቀኑ የሚያልቀው ህይወት ፋታ የነሳቸው የእርሻዉ ሰራ አሰኪያጅ ለአስቸኳይ እርዳታ ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅት ግን ሀይሉ ሻወልና ካሳ ከበደ የሰጡት መልስ "የተረፈው ይበቃል" ነበር። ዛሬ ቅቤ አንጓች ሆነው ያን ህዝብ ነጻ ሊያ፟ጡ ደፋ ቀና ሲሉ መመልከት ምንኛ ያስገርማል። ዛሬ ካሳና ሃይሉ የዴሞክራሲ ጠበብት ሆነው ስለ መብትና ነጻነት ሲያወሩ መሰማት ምንኛ ያሰቃል።

የትናንቱን ግፍና መከራ አድበስብሳችሁ የወገኖቻችን ሰቃይና ሞት አዘናግታችሁ ኢሰፓና መሰሎቹን በቅንጅት ተክታችሁ ዳግማዊ ረመጥ የምታዘገጁልን የተጠናወታችሁን የስልጣን ሱሰ ለማርካታ መሆኑን ጠንቅቀን እንረዳለን። ቅንጅት ያላው አላማ አንድ ብቻ ነው። በስልጣን ላይ ያለውን ኢህአዴግ ከስልጣን አስወግዶ በወህኒ የሚገኙ የደርግ ነብሰ-ገዳዮችን ከእስር ፈቶ በስደት ላይ የሚገኙ ዘር-አጥፌዎችን ወደ ሀገርቤት መለሶ አንድ ወጥ የፖለቲካ ሞኖፖሊ በመፍጠር የኢትዮጵያን ህዝብ ለሌላ እልቂት ማዘጋጀት ነው። ከካድሬወቹ ብዛት የተነሳ ድርጅታዊ ትምክህት የወጠረው ቅንጅት ከጅምሩ በሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚያሳየው ንቀት ለሚኖረን ዴሞክራሲያዊ ሂደትና የሁሉም ህዝብ የሰላም የብልጽግና የሰብአዊ መብቶች መከበር መሰናክል ነው። ይህ ገጽታና ባህሪው ደግሞ ከእናት ድርጅቱ ከኢሰፓ የወረሰው ሊለወጥና ሊቀየር የማይችል ተፈጥሮው መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ቅንጅት የሀገራችን ሰላም አጥፍቶ እልቂትን አሰፋፍቶ ድህነትን አባብሶ አምባገነንነትን አጎልብቶ በሚፈጥረው አፋኝ ስርአት ዴሞክራሲን ቀብሮ አንድነትን አናግቶ ጅምር ግንባታዎችን አደናቅፎ ለባሰ ድህነት ሊጋብዘን የተዘጋጀ የነብሰ-ገዳዮች ቡድንና ጥርቅም ነው። በዴሞክራሲ በርኖስ በድናቸውን ሸፍነው በመላው አለም ተበትነው የሚገኙ ነብሰ-ገዳዮች እንደገና ወደኢትዮጵያ ተመልሰው ግድያና ጭፍጨፋቸውን መቀጠል

**የሚችሉትና በእስር ላይ የሚገኙ እንደነ መላኩ ተፈራ አይነት ፋሽሽቶችን ከህዝባዊ ቅጣት የሚያተርፉት ቅንጅት አይናችን ሸፍኖ አፋችን ለጉሞ ስልጣን ላይ ሲፈናጠጥ ብቻ በመሆኑ ጠንቅቀን ልንጠባበቅ ይገባል።**

**ነጻነት ተሰማ**
**ዋሽንግተን ዲ.ሲ.**
August 18, 2007